# በዶ/ር ብርሃኑ ነጋ መጽሐፍ ላይ የቀረበ አስተያየት

ከልደቱ አያሌው

## መግቢያ

የዶ/ር ብርሃኑን መፅሐፍ በጥሞናና በእርጋታ አነበብኩት፡፡ በጥቅሉ መፀሐፉ ብዙ መረጃዎችን የያዘ ጠቃሚ ሰነድ ነው፡፡ ይህ መፅሐፍ ዶ/ር ብርሃኑ ምን ያህል ጕበዝ ደራሲና በተለይም በገፀ ባህሪ (character) አሳሳላቸው እጅግ የተካኑ መሆናቸውን ያሳያል፡፡

ዶ/ር ብርሃኑ መፅሐፍ የማሳተማቸውን ዜና ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁት አሜሪካን አገር በስራ ጉብኝት ላይ ሆኜ ነበር፡፡ ይህ ዜና ለእኔ በሁለት ምክንያቶች በጣም አስደሳች ነበር፡፡ የመጀመሪያው ምክኒያቴ ዶ/ር ብርሃኑ በቅንጅቱ ውስጥ ከነበራቸው ጉልህ ተሳትፎ አንፃር በቅንጅቱ ዙሪያ የነበረውን ሂደት የሚገልፅ ትክክለኛ መረጃ ይሰጣሉ ከሚል አጠቃላይ እምነት በመነሳት ሲሆን - ሁለተኛው ምክኒያቴ የወቅቱን የትግል ሂደትና ቅንጅቱን በሚመለከት እኔ በቅርቡ ለአሳተምኩት መፅሐፍ ዶ/ር ብርሃኑ ቀጥተኛ ትችት ሊያቀርቡ ይችላሉ የሚል ግምት ስለነበረኝ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ከውጭ አገር ወደ አገር ቤት እንደተመለስኩ መፅሐፉን ገዝቼ አነበብኩት፡፡ ነገር ግን ለሁለቱም ቀዳሚ ግምቶች አጥጋቢ ምላሽ ሳላገኝ ቀረሁ፡፡ የቅንጅቱን አጠቃላይ ሂደት በሚመለከት መፅሐፉ በርካታ መረጃዎችንና ሐቆችን ያካተተ መሆኑን መካድ ባይቻልም በዚያው መጠን በጣም በርካታ ተዛብተው፣ ተጣመው፣ ተጋነው፣ ተቀንሰው፣ ተጨምረው፣ ከዚያም በላይ በሐሰት የቀረቡ ሃሣቦችን ያካተተ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

እኔ ያሳተምኩትን መፅሐፍ በሚመለከትም ይህ ከ600 በላይ ገፆችን ያካተተ ሰፊ መፅሐፍ አንድም ቀጥተኛ ትችትና አስተያየት ሳይሰጥ አልፎአል፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ ይህን ለማድረግ ለምን እንደፈለጉ አንባቢ እራሱን መጠየቁ የሚቀር አይመስለኝም፡፡ ምንአልባት ዶ/ር ብርሃኑ የልደቱን መፅሐፍ ሳያገኙት ቀርተው ወይንም ንቀው ሳያነቡት ቀርተዋል ተብሎ እንዳይታሰብ መፅሐፉን ያነበቡት ስለመሆናቸው ሁለት ቦታ ላይ በተዘዋዋሪ ጠቁመው አልፈዋል፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ ይህንን አይነት ጥቆማ በፅሁፋቸው ውስጥ ሳያቀርቡ አልፈው ቢሆን እንኳ በሁለቱም ምክኒያቶች የልደቱን መፅሐፍ ሳያነቡት ይቀራሉ ብሎ መገመት ያስቸግራል፡፡ መፅሐፉን አላገኙት ይሆናል እንዳይባል እስር ቤት ውስጥ ያሉ ሰዎች መፅሐፍ አስገብተው የማንበብ መብትና እድል እንዳላቸው በዶ/ር ብርሃኑ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱት ከተለያዩ መፅሐፎች የተወሰዱ ቀጥተኛና እረዣዥም ጥቅሶች በራሳቸው ማረጋገጫዎች ናቸው፡፡ መፅሐፉን በንቀት ሳያነቡት ቀርተው ይሆናል እንዳይባልም ዶ/ር ብርሃኑ አይደለም ቀርቶ የልደቱን መፅሐፍ ንቀው መተውና ከልደቱ አፍ የወጡ ቃላቶችንና ስለ ልደቱ የተወሩ ማናቸውንም ዓይነት ሃሜቶች ንቀው እንደማያልፉ በመፅሐፋቸው ውስጥ ደጋግመው አሳይተዋል፡፡ ስለዚህ በእኔ እምነት ዶ/ር ብርሃኑ የእኔን መፅሐፍ ቀጥተኛ በሆነ መንገድ አንቀፅ እየጠቀሱ መተቸትን የሚጠቅምና የሚያዋጣ ስልት ሆኖ እንዳላገኙት ይሰማኛል፡፡ ያም ሆነ ይህ ዶ/ር ብርሃኑ እራሳቸው ያዋጣኛል ብለው በመረጡት ስልት የፃፉት ይህ መፅሐፍ ከእኔ

ከግሌ፣ አባል ሆኜ ከምታገልለት ከኢዴአፓ-መድህንም ሆነ ከአጠቃላዩ የትግል እንቅስቃሴ አንፃር በብዙ ጐኑ ጠቃሚ እንጂ ጐጂ ሆኖ አላገኙሁትም፡፡ በኔ መፅሐፍ ላይ የሰፈሩትንም ሆነ በተለያዩ ጊዜ የኢዴአፓ-መድህን አመራሮች ስለቅንጅቱ የምንናገራቸውን አንዳንድ አስደንጋጭ ሃቆች አምነው ለመቀበል ተቸግረው የነበሩ አንዳንድ ሰዎች ይህንን የዶ/ር ብርሃኑ መፅሐፍ ካነበቡ በኋላ በፈጠራ የፃፍነው ወይም የተናገርነው ነገር እንደሌለ ማረጋገጣቸውን በስልክም በአካልም ገልጸውልናል፡፡ ስለሆነም አቅሙ የፈቀደለት ገዝቶ፣ ያልቻለም ተውሶ ይህንን የዶ/ር ብርሃኑን መፅሐፍ ቢያነበው በእኔ በኩል እጅግ ጠቃሚ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ አንባቢ ይህንን እኔ በዶ/ር ብርሃኑ መፅሐፍ ላይ የማቀርበውን ትችት ተገቢነትና ትክክለኛነት በውል ሊረዳልኝ የሚቻለውም በቅድሚያ የእሳቸውን መፅሐፍ ሲያነቡ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

አንደኛ - ስለእኔና ስለሌሎች የትግል ጓደኞቼ ሆነ ስለኢዴአፓ-መድህን ለአለፈው ሙሉ አንድ አመት በሬዲዮ፣ በጋዜጣ፣ በኢንተርኔትና በየመንደሩ በተለያዩ ሰዎች ሲነዛ የከረመው የፈጠራ አሉባልታ ምን ያህል ከተጨባጩ እውነታ ጋር የማይጣጣምና የማይገናኝ ስለመሆኑ የዶ/ር ብርሃኑ መፅሐፍ በራሱ ማረጋገጫ ሆኖ ቀርቧል፡፡ በዚህም ምክኒያት ዶ/ር ብርሃኑ መፅሐፍ አሳተሙ ሲባል የልደቱንና የኢዴአፓ-መድህንን “ወያኔነት” የሚያረጋግጥ ተጨባጭ መረጃ ይገኛል ብለው የገመቱ አንዳንድ የዋህ ግለሰቦች መፅሐፉን አንብበው የተመኙትን ሳያገኙ በመቅረታቸው ማፈራቸውን እየታዘብኩ ነው፡፡ እነዚህ ግለሰቦች ከዚህ ቀደም “ልደቱና ባንዳዊ ስሌቱ” በሚል ርዕስ የታተመውን መፅሐፍ ተመሳሳይ ጥቅም እናገኝበታለን ብለው ቋምጠው ካነበቡት በኋላ መፅሐፉ ቅንጣት ያህል ቁምነገር ያልያዘ የትርኪ ምርኪ ክምችት መሆኑን ሲገነዘቡ እንደገና ያን መፅሐፍ ሆን ብሎ ያሳተመው ልደቱ ነው የሚል ወሬ ሲያስወሩ ሰምቼ ነበር፡፡ እነዚህ ግለሰቦች በዶ/ር ብርሃኑ መፅሐፍም ውስጥ ስለእኔ “ወያኔነት” ከአሉሽ አሉሽ ያለፈ አንድም ተጨባጭ መረጃ ሳያገኙ ሲቀሩ በጥላቻ በተሞላው ተስፈኝነታቸው ምን ያህል ሊያፍሩ እንደሚችሉ መገመት አያስቸግርም፡፡ እኔ “የአረም እርሻ”ን አሳትሜ ለንባብ ካቀረብኩ በኋላ አንባቢያን በመፅሐፌ ዙሪያ ያላቸውን አስተያየት እንዲሰጡኝ በዚያው በመፅሐፌ ላይ አድራሻዬን በግልፅ ማስቀመጤ ይታወሳል፡፡ በዚህም መሠረት እስካሁን በስልክ፣ በፖስታና በኢ-ሜል በሺ የሚቆጠሩ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ አስተያየቶች የተሰጡኝ ሲሆን እስካሁን ድረስ ከአንድ የእርምት አስተያየት በስተቀር በመፅሐፍህ ውስጥ ያሰፈርከው ይህ ሃሣብ ውሸት ነው ብሎ አስተያየት የሰጠኝ (ዶ/ር ብርሃኑን ጨምሮ) ሰው የለም፡፡ ደረሰኝ ያልኩት አንድ የእርምት አስተያየት “አዲስ ዜና” በመባል የሚታወቀውና የእኔን ስም በማጥፋት ተግ ባር ላይ ተሰማርቶ የነበረው ጋዜጣ ቀደም ሲል በእነ ዶ/ር ብርሃኑና በኢንጂነር ኃይሉ ሻዎል የአክሲዮን ባለቤትነት የተቋቋመ ጋዜጣ እንደነበር በገለፅኩት ጉዳይ ላይ የቀረበ ማስተካከያ ነበር፡፡ ማስተካከያው የአክሲዎን ባለድርሻው እንጂነር ኃይሉ ሻዎል ሳይሆኑ ልጃቸው ዶ/ር ሻዎል ኃይሉ ናቸው ተብሎ የቀረበ ነው፡፡ በኋላ ላይ ባደረግሁት የማጣራት ጥረት እርማቱ ትክክል እንደነበር ስለአረጋገጥኩ በዚህ አጋጣሚ ለሠራሁት ስህተት አንባቢን ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡ በእርግጥ ስህተቱን የሰራሁት ሆን ብዬ ሳይሆን እራሳቸው ኢንጂነር ኃይሉ ሻዎል በአንድ ወቅት በዚህ “ABC” በመባል በሚታወቀው የሚዲያ ድርጅት ውስጥ ከፍተኛ የአክሲዎን ድርሻ እንዳላቸው ሲያወሩ ስለሰማሁ ነበር፡፡ ዞሮ ዞሮ ከሳቸው

የሰማሁትን አባባል ተጨማሪ ማጣራት ሳላደርግ በቀጥታ መፃፌ ስህተት ከመሆን ሊድን አይችልም፡፡

ሁለተኛ - ይህ የዶ/ር ብርሃኑ መፅሐፍ ከነግድፈቶቹም ቢሆን በቅንጅቱ ውስጥ በተለያዩ ፓርቲዎችና ግለሰቦች የነበሩትን የአስተሳሰብ ልዩነቶች በዝርዝር ያቀረበና የፖለቲካ አካሄድ ለሚገባው አንባቢ በዚያ ሂደት ውስጥ የማን አመለካከትና የትግል ስልት ትክክለኛና የተሻለ እንደነበር በግልፅ የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ እረገድ በየትኛው መመዘኛ እኔም ሆንኩ በአባልነት የምሰራበት ኢዴአፓ-መድህን በዶ/ር ብርሃኑ መፅሐፍ ተጠቃሚ እንጂ ተጐጂዎች አይደለንም፡፡

ሦስተኛ - ይህ የዶ/ር ብርሃኑ መፅሐፍ እኔም ሆንኩ ሌሎች የኢዴአፓ-መድህን አመራር አባላት ከእስካሁኑ በተሻለ ሁኔታና መጠን በቅንጅቱ ዙሪያ ያለፍንባቸውን ሃቆች ለሕዝብ እንድንገልፅ የተሻለ ነፃነትና እድል የሚሰጥ ነው፡፡ ብዙዎቹ የቅንጅቱ አመራሮች በአስከፊ ሁኔታ በወህኒ እየማቀቁ ስለሚገኙ፣ የታሰሩ ሰዎችም እንዲህ እንደአሁን 614 ገፅ ያለው መፅሐፍ አሣትመው የራሳቸውን አቋም ለሕዝብ የማቅረብ እድሉ ይኖራቸዋል ብለን ስላልገመትን፣ በአገራችንም "የሞተ ሰው አንገተ ቅጥል ነው" የሚል ልማዳዊ አስተሳሰብ እንደመኖሩ ሕብረተሰቡ ከኛ ይልቅ ለታሰሩ ሰዎች የሚኖረውን ሐዘኔታና አክብሮት ግምት ውስጥ በማስገባት፣ አንዳንድ እራሳችን ለመከላከል ብለን ለሕዝብ የምናቀርባቸው ሐቆችም በሌሎች ኃይሎች መጠቀሚያነት ውሎ የታሰሩትን የቅንጅት ሰዎች የበለጠ የሚጐዳ እንዳይሆን በመስጋት፣ በአጠቃላይም በቅንጅቱ ዙሪያ የነበረውን ገመናችን ሁሉ በአንድ ጊዜ ሜዳ ላይ አውጥቶ መዘርገፍ በሕዝቡ ሞራል ላይ ጉዳት እንዳያስከትል በመስጋት የራሳችንን ነፃነት በራሳችን ውሳኔ ገድበነው ቆይተናል፡፡ "የአረም እርሻ"ን አሳትሜ ለንባብ ሳቀርብ በቅንጅት ውስጥ እንዴት እንዲህ ዓይነት አስቀያሚ ሁኔታ ሊኖር ይችላል ብለው ለማመን የተቸገሩና የተደናገጡ በርካታ ሰዎች ያጋጠሙኝን ያህል - በርካታ በተለይም በኢዴአፓ-መድህን ዙሪያ የነበሩና የቅንጅቱን የውስጥ ገመና ጠንቅቀው የሚያውቁ የፓርቲ አባላት በ"አረም እርሻ" የተለሳለሰ አቀራረብ በጣም ተቆጭተው ቅሬታቸውን ገልፀውልኛል፡፡ አንዳንዶቹም ቅሬታቸውን ከመግለፅ አልፈው አኩርፈውኛል፡፡ እነዚህ ያኰረፉኝ ወዳጆቼ የሚያቀርቡልኝ ትችት - "ከፖለቲካ መድረኩ እንድትገለል ብቻ ሳይሆን ሕዝብ በስሜት ተነሳስቶ ሕይወትህን እንዲያጠፋ ዘመቻ ላደረጉብህ ሰዎች ምን ትርጉም ሊኖረው ነው ይህን ያህል ነገሮችን አለባብሰህ ያቀረብከው -? ከዚህስ በላይ ምን እስኪያደርጉህ ነው የምትጠብቀው?" የሚል ነበር፡፡ ለዚህ ዓይነቱ አስተያየት እኔ ስሰጥ የነበረው መልስ "እነሱ በሄዱበት መንገድ ሄደን እራሳችን አሳንሰን ማሳየት የለብንም፡፡ ከነሱ የተሻልን የዓላማ ሰዎችና የትግል ባህሪ ያለን መሆኑን ለማሳየት የምንችለው ይህንን የስሜታዊነት ወቅት በትዕግስት ማሳለፍና እኛ ከምንናገረው በላይ የትግሉ ሂደት በራሱ ትክክለኛውን መልስ ለሕዝቡ እንዲሰጥ በማድረግ ነው፡፡ በአንድ ጊዜ የምናውቀውን ሁሉ ከመዘርገፍም ወደፊት ጊዜና ሁኔታዎችን እየጠበቅን የምንጠቀምበትን ስንቅ መቆጠቡ የተሻለ ነው" የሚል ነበር፡፡ በእኔ እምነት እንደልባችን እንድንናገር ከማያስችሉን ከላይ ከጠቀስኳቸው ምክንያቶች ውስጥ ብዙዎቹ ዛሬም በራሳችን ነፃነት ላይ ገደብ ጥለን እንድንቀጥል የሚያስገድዱን በመሆናቸው አሁንም መቆጠብ የሚገባን ስንቅ እንዳለ ባምንም በተወሰነ ደረጃ

ከእስካሁኑ በተሻለ ሁኔታና መጠን የምናውቀውን እንድንናገር የዶ/ር ብርሃኑ መጽሐፍ እድል ፈጥሮልናል ብዬ አምናለሁ፡፡ ይህ በዶ/ር ብርሃኑ መፅሐፍ ላይ የምሰጠው አስተያየት ይህንን መሠረታዊ ወቅታዊ አቋም መሠረት በማድረግ ሲሆን - ነገር ግን አሁንም ቢሆን የምሰጣቸው አስተያየቶች ዶ/ር ብርሃኑ በመፅሐፋቸው ካሰፈሩአቸው አከራካሪ ጉዳዮች (Issues) እና ኢዴአፓ-መድህንን፣ እኔንና ሌሎች የኢዴአፓ-መድህን አመራሮችን በሚመለከት ከሠነዘሯቸው አስተያየቶች ቢቻል ያልወጡ፣ አሊያም ያልራቁ ጉዳዮች ላይ ይሆናል፡፡ አሁንም እንደ በፊቱ እንደ ዶ/ር ብርሃኑ ሃሣባቸውን ፅፈው ለማስነበብ ያልቻሉት የቅንጅት አመራሮች ላይ የምሰጣቸው አስተያየቶች ቁጥብ እንዲሆኑ የምችለውን ጥረት አደርጋለሁ፡፡

ይህንን ትችት ሳቀርብም በመፅሐፉ ውስጥ ያሉትን በርካታ ጠቃሚ ቁምነገሮችና እውነተኛ ዘገባዎች እንደሌሉ በመቁጠርና አጠቃላይ የመፅሐፉን ይዘት ለማንኳሰስ እንዳልሆነ አንባቢ በቅድሚያ እንዲረዳልኝ እፈልጋለሁ፡፡ በእርግጠኛነት መናገር የምችለው እንዳሉ ልቀበላቸው የምችል፣ ትክለኛና ተገቢ የሆኑ አስተያየቶችና ዘገባዎች በዚህ የዶ/ር ብርሃኑ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ መሆኑ ነው፡፡ በእነዚህ አስተያየቶችና ዘገባዎች ላይ አስተያየት ሳልሰጥ የማልፈው እኔም የምጋራቸውና የምቀበላቸው ስለሆኑ እንጂ ጠቃሚ ወይንም ትክክል አይደሉም ብዬ ስለማምን አይደለም፡፡ በእርግጥ በአንዳንድ ችግር ባለባቸው ነጥቦች ላይም የኔ አስተያየት መስጠት መሠረታዊ ለውጥ አያስከትልም ብዬ ካመንኩና በአንባቢ ግንዛቤ ላይ ያን ያህል ተፅእኖ አያስከትሉም ብዬ ከገመትኩ አስተያየት ሳልሰጥባቸው አልፋለሁ፡፡ በዋናነት የትችቴ ወይንም የአስተያየቴ ትኩረት በአራት ዋና ዋና ጉዳዮች ዙሪያ ላይ ይሆናል፡፡

የመጀመሪያው - በአጠቃላይ የመፅሐፉን ይዘት እንደገመገምኩት ዶ/ር ብርሃኑ ማስተላለፍ የሞከሩት ዋና መልእክት በግንቦቱ ምርጫ ሕዝቡና ተቃዋሚዎች በተለይም ቅንጅቱ ያገኛቸው አጠቃላይ ውጤቶች ሊገኙ የቻሉት በዋናነት እራሳቸው ዶ/ር ብርሃኑና ቀስተዳመና አዲስ አስተሳሰብና የአሰራር ስልት ፈጥረው ትግሉን በመቀላቀላቸው እንደሆነ አድርገው ማሳየት ነው፡፡ የእኔም የመጀመሪያ ትችትና አስተያየት የሚያተኩረው ይህ አይነቱ የዶ/ር ብርሃኑ አስተሳሰብ ምን ያህል እውነት መሆኑንና አለመሆኑን ለአንባቢ በማሳየት ነው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ዶ/ር ብርሃኑ በሰፊው ትኩረት ሰጥተው የፃፉት በቅንጅቱ ውስጥ በነበሩ የተለያዩ ውሳኔ የሚጠይቁ አከራካሪ ጉዳዮች ላይ ማለትም የቅንጅቱን መሪ በመምረጥ፣ በምርጫው ልናገኘው የምንችለውን ውጤት አስቀድሞ በመገምገም፣ የምርጫ ችግሮችን በማጣራቱ ሂደት፣ የሕዝቡን ሰላማዊ ትግል በመምራት እረገድ፣ በጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት ጥያቄ አቀራረብ፤ ፓርላማ በመግባትና ባለመግባት ጥያቄና በቅንጅቱ የውህደት ጥያቄ ዙሪያ ዶ/ር ብርሃኑ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የወሰዷቸው አቋሞች ትክክል እንደነበሩ ማሳየት ነው፡፡ የእኔም ሁለተኛ ክፍል ትችትና አስተያየት ትኩረት የሚሰጠው በእነዚህ አከራካሪ ጉዳዮች ላይ የማን አቋም ትክክል እንደነበር ለአንባቢ ለማሳየት ነው፡፡

በሦስተኛ ደረጃ ዶ/ር ብርሃኑ ትኩረት ሰጥተው በእያንዳንዱ አንቀፅ፣ ሲችሉም በየአንዳንዱ የመፅሐፋቸው ገፅ ለአንባቢ ሊያስተላልፉ የሞከሩት

መልእክት በአንድ በኩል እሳቸው ምን ያህል ብልህ፣ ታማኝ፣ ግልፅና መርህን መሠረት ያደረጉ ደፋር ፖለቲከኛ እንደሆኑ ማሳየት ሲሆን - ከዚህ በተፃራሪ ደግሞ ሌሎቻችን የቅንጅቱ አመራሮች አንዳንዶቻችን አምባገነኖች፣ የሥልጣን ጥመኞች፣ የፖለቲካ ማይሞች፣ መሰሪዎች፣ አንዳንዶቻችንም ከዚያም በላይ ልዩና ድብቅ ተልዕኮ ያለን ሰዎች እንደሆንን አድርጐ ለማሳየት የሚያስችላቸውን ሃሣብ ሁሉ እያዛቡ፣ እያጣመሙ፣ እያጋነኑ፣ እያቀነሱ፣ እየጨመሩ፣ ከዚያም በላይ ሲያስፈልግ ነጭ ውሸት እየዋሹ ማቅረብ ነው፡፡ የእኔም ሦስተኛው የትችት ክፍል ይህንን ተዛብቶ፣ ተጋኖ፣ ተጨምሮ፣ ተቀንሶና ተዋሽቶ የቀረበውን ሃሣብ አስተካክሎ ለአንባቢ ማቅረብ ነው፡፡ በዚህ የማስተካከያ ጥረቴ አንባቢ ሌላ ብዥታና መደናገር ውስጥ እንዳይገባም የተጠቀሱትን ሃሣቦች ለማስተባበል የምፈልገው በአብዛኛው አዲስ መረጃ በመስጠት አይሆንም፡፡ እራሳቸው ዶ/ር ብርሃኑ በዚህ መፅሐፋቸው ውስጥ በተለያዩ ስሜቶችና አንቀፆች ላይ ሆነው ያቀረቧቸውን የተዘበራረቁና እርስ በርሳቸው የሚጋጩ ሃሣቦች መልሼ በማቅረብ እውነቱን አንባቢ እንዲረዳው ለማድረግ እጥራለሁ፡፡

አራተኛውና የመጨረሻው የዶ/ር ብርሃኑ መፅሐፍ ትኩረት የወደፊቱ የአገራችን ሠላማዊ ትግል እንዴት ይቀጥል? ለሚለው ጥያቄ በቁንፅልም ቢሆን መልስ ለመስጠት የሚሞክር ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የምንገኝ የፖለቲካ ኃይሎች ከምንም ነገር በላይ ትኩረትና ቅድሚያ ሰጥተን ልንወያይበት የሚገባን ቁምነገር በዚህ አጀንዳ ዙሪያ ነው ብዬ ስለማምን የእኔም የዚህ ፅሁፍ የመጨረሻ ክፍል ከዶ/ር ብርሃኑ አስተሳሰብ በመነሳት ጠቅለል ባለ መልኩ በዚህ ወቅታዊ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ያለኝን የግል አስተያየት መስጠት ይሆናል፡፡

## ክፍል አንድ

### 1. የ1997 ዓ.ምቱ የምርጫ “ውጤት” የማን ነው?

በዚህ ርዕስ ላይ “ውጤት” የሚለውን ቃል በትምህርተ ጥቅስ ውስጥ ያስቀመጥኩት ያለምንም ምክኒያት አይደለም፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎች (በተለይም በቅንጅቱ ዙሪያ የነበርን) ዛሬ ላይ ቆመን ከግንቦት 97 ዓ.ም. ምርጫ በፊት የነበርንበትን ደረጃ ዛሬ ከምንገኝበት ሁኔታ ጋር ሳነፃፅረው ለእኔ በዚያ ምርጫ ላይ ያገኘነው “ውጤት” ከዛሬው ተጨባጭ ሁኔታችን አንፃር “ውጤት” መሆኑና አለመሆኑ በጣም አከራካሪ ነው፡፡ ምክንያቱም በዚያ ምርጫ ያገኘነው ውጤት በትክክልም ውጤት ሆኖ ሊገኝ የሚችለው በአሁኑ ወቅት በዚያ ምርጫ ያገኘነውን ውጤት በአግባቡ በእጃችን ይዘን እየተጠቀምንበት ቢሆን ነበር፡፡ በቅንጅት ዙሪያ በፓርቲ አባልነትም ሆነ በደጋፊነት ተሳታፊ የነበርን ሰዎች ዛሬ ላይ ቆመን ለሚቀጥሉት ጥያቄዎች የየራሳችንን መልስ ብንሰጥ “ውጤቱ” ውጤት መሆኑንና አለመሆኑ ለመገንዘብ አስቸጋሪ አይመስለኝም፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከግንቦት 7 በፊት የነበረን ድርጅታዊ ጥንካሬ ዛሬ አለ ወይ? ከምርጫው በፊት በትግሉ ሂደት ተሳታፊ የነበረው ቅንጅትም ሆነ ከአባል ድርጅቶቹ ውስጥ መኢአድ፣ ቀስተ ደመና፣ ኢዴሊ ዛሬ እንደ አንድ የፖለቲካ ድርጅት በህጋዊና ሰላማዊ የትግል ሂደቱ ውስጥ አሉ ወይ? አብዛኛዎቹ በቅንጅቱ ዙሪያ የነበሩ አመራሮች ወደ ወህኒ መወርወራቸው - አባላትና ደጋፊዎች ከስራቸው፣ ከአካባቢያቸውና ከአገራቸው ለቀው መሰደዳቸው በራሱ በጐ “ውጤት” ነው ወይ? ከግንቦት 7ቱ ምርጫ በፊት በስራ ላይ የነበሩ

በርካታ የግል ፕሬሶች ዛሬ በስራ አሉ ወይ? ከግንቦት 7ቱ ምርጫ በፊት በሕዝቡ ውስጥ የነበረው በሰላማዊና በምርጫ ሂደት ለውጥ የማምጣት ስሜትና ፍላጎት ዛሬ አለ ወይ? ሕዝባችን በግንቦት 7ቱ ምርጫ ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍሎ የመረጣቸው ወኪሎቹ ዛሬ በየተመረጡበት ምክር ቤት ገብተው መራጩን ሕዝብ እያገለገሉት ነው ወይ? ፈፅሞ በማያከራክርና በማያጠራጥር ሁኔታ የሚፈልገውን ወኪል መምረጥ የቻለው የአዲስ አበባ ሕዝብ ዛሬ በመረጣቸው ወኪሎቹ እየተዳደረ ነው ወይ? በአጠቃላይ አነጋገር ከምርጫው በፊት የኢትዮጵያ ሕዝብ መንግሥታዊ ለውጥ ለማምጣት ያካሂድ የነበረው የፖለቲካ ትግል በአንድ ጊዜ ተንኮታኩቶ ዛሬ እስረኛ በማስፈታት ትግል አልተወሰነም ወይ?

በእኔ በኩል ለእነዚህ ጥያቄዎች የራሴን መልስ በመስጠት የደረስኩበት ድምዳሜ የችግሩ ምንጭና ተጠያቂ ማንም ይሁን ማን የኢትዮጳያ ሕዝብ የፖለቲካ ትግል ግንቦት 7/97ዓ.ም. ያገኘው "ውጤት"፣ ውጤት ሳይሆን ውድቀት ነው፡፡ ለጊዜው ይህንን አከራካሪ ጉዳይና ከምርጫው በኋላ የተከሰቱትን ውጣ ውረዶች ከዶ/ር ብርሃኑ አቀራረብ አንፃር "ውጤቱን" በጥሬው ውጤት ነው ብለን በመቀበል የዚያ ውጤት ባለቤት ማን ነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እንሞክር፡፡ በእኔ እምነት አንድ የፖለቲካ ድርጅት በአንድ አገራዊ ምርጫ ተወዳድሮ ለማሸነፍ የሚበቃው ሁለት መሠረታዊ ሁኔታዎችን ማለትም በሕዝብ ተቀባይነት ያለው ጠቃሚ አስተሳሰብና ሁለንተናዊ ድርጅታዊ ጥንካሬ ይዞ ሲገኝ ነው፡፡ ከነዚህ ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች አንፃር ዶ/ር ብርሃኑ ለምርጫው ውጤት መገኘት "እኔና ቀስተዳመና አመጣነው" የሚሉትን አዲስ አስተሳሰብና ድርጅታዊ ጥንካሬ ለመገምገም እንሞክር፡፡

## 1.1. <u>ቅንጅት በምርጫው ይዞት የቀረበው አጀንዳ (አስተሳሰብ) የማን ነው?</u>

ዶ/ር ብርሃኑ በመፅሐፋቸው ምዕራፍ 5 ገፅ 254 እንዲህ ይላሉ - "---በኢትዮጵያችን እስከ ምርጫ 97 ድረስ የነበረው የተቃውሞ ፖለቲካ በአብዛኛው ለኢህአዴግ አፀፋ መላሽ (Reactive) ፖለቲካ እንጂ የራሱን ራዕይ በግልፅ አቀናብሮና አስቀምጦ ለዚያ ራዕይ ተግባራዊነት የመታገል አዎንታዊ (positive) ፖለቲካ አልነበረም ለማለት ያስደፍራል፡፡ እንደማንኛውም ኢ-ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የኢህአዴግ መንግሥት ብዙ ሰዎችን በመብታቸውም በኢኮኖሚ ጥቅማቸውም ጐድቷቸዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ ኢህአዴግ እንዲወድቅላቸው ይፈልጋሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥም ደፈር ያሉት አንዱን ወይም ሌላውን የተቃውሞ ድርጅት ይቀላቀላሉ፡፡"

በዚህ የዶ/ር ብርሃኑ አባባል በግልፅ እንደሰፈረው ከግንቦት 97ዓ.ም. ምርጫ በፊት ለአለፉት 14 ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ ትግል ስናደርግ የነበርነው ፓርቲዎች በሙሉ ኢህአዴግን ለመቃወም የተቋቋምን እንጂ ምንም አይነት አገራዊ ራዕይ የሌለን ነን፡፡ እንደ ዶ/ር ብርሃኑ አባባል ለ14 ዓመታት ትግሉ ውስጥ የነበርን ሰዎች ትግሉን የተቀላቀልነው ኢህአዴግ መብታችንንና ኢኮኖሚያዊ ጥቅማችንን ስለጐዳውና በዚህም ምክኒያት ሥርዓቱ እንዲወድቅልን ስለምንፈልግ እንጂ ከዚያ ያለፈ ለአገር የሚበጅ ፖለቲካዊ አጀንዳ የለንም፡፡ በዚህ የዶ/ር ብርሃኑ እይታ ለአለፉት 14 ዓመታት በመዐሕድ፣ በኦነግ፣ በኢዲዩ፣ በደቡብ ህብረት፣ በመኢአድ፣

በኢዴአፓ-መድህን፣ በኦብኮ እና በሌሎችም ፓርቲዎች አባልነታቸው የተገደሉት፣ በእስር የማቀቁት፣ አገር ጥለው የተሰደዱት በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሁሉ የግል መብትና ጥቅማቸው ስለተነካ ትግሉን የተቀላቀሉ እንጂ ፖለቲካዊ ራዕይ ያላቸው ሰዎች አይደሉም፡፡ በዶ/ር ብርሃኑ አገላለፅ እነዚህን ሰዎች ከሌላው ሕዝብ የሚለያቸው አንድ ነገር ቢኖር የፖለቲካ ድርጅት አባል ለመሆን ደፋር- ያሉ ግለሰቦች መሆናቸው ብቻ ነው፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ በመፅሐፋቸው ደግመው ደጋግመው እንደገለፁት ራዕይ ያለው የፖለቲካ ትግል በአገራችን የተጀመረው እርሳቸው የፖለቲካ ትግሉን ሲቀላቀሉ በ1997ዓ.ም. ነው፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ እንዲህ አይነቱን እጅግ ስሜታዊ፣ ንቀትና ይሉኝታ ቢስነት የተሞላበት አስተያየት ከመስጠታቸው በፊት እሩቅ ሳይሄዱ እርሳቸው በአሁኑ ወቅት የሚገኙበትን እስር ቤት የቅርብ ታሪክ ቢያጠኑና በእምነታቸው ምክኒያት በዚያ እስር ቤት ሲማቅቁ ለእልፈተ ሕይወት የበቁትን ፕሮፌሰር አስራትን፣ አሁንም በዚያው እስር ቤት እየማቀቁ የሚገኙትን እነ አበራ የማነአብና እነ ፊታውራሪ መኰንን ዱሬን ቢያስታውሱ ኖሮ እንደዚህ ዓይነት እራሳቸውን ግምት ውስጥ የሚጥል አስተያየት ባልሰጡ ነበር፡፡ ቢያንስ ቢያንስ በአሁኑ ወቅት ከእርሳቸው ጋር በቅንጅት ስም ታስረው የሚገኙት የመኢአድና የኢዴአፓ-መድህን አባላት እርሳቸው የሥልጣን መፈናጠጫው ወቅት የተዳረሰ መስሏቸው ትግሉን ከተቀላቀሉበት ከ97ዓ.ም. በፊት በ14 ዓመታት ምን ያህል መስዋዕትነት እንደከፈሉ ቢረዱና ለዚህ መስዋዕትነት ለከፈሉበት ዓላማ መጠነኛ ክብር ሊሰጡ በተገባ ነበር፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ ትናንት በእስር ቤት ለተዋወቋቸው ለእነ አቶ እሰዬ አብርሃ የበለጠ ክብር ሰጥተው መፅሐፋቸውን በመታሰቢያነት ከማቅረባቸው በፊት ለእራሳቸው የትግል አጋሮች ተገቢውን ክብር ቢሰጡ መልካም ነበር፡፡ ለአለፉት 14 ዓመታት ኢሕአዴግ ደጋግሞ ሲለን እንደነበረው የኢትዮጵያን ተቃዋሚ ፓርቲዎች በጥቅሉ ዓላማና ራዕይ የሌለን አድርጐ ማቅረብ ከኛ በፖለቲካ ትግሉ ተሳታፊዎች አልፎ የሕዝቡን የ14 ዓመት የትግል ተሣትፎ ማንቋሸሽ ነው፡፡

በእርግጥ ዶ/ር ብርሃኑ ይህን ቢሉ ብዙም አይፈርድባቸውም፡፡ እርሳቸው የፖለቲካ ትግሉን ከተቀላቀሉበት ከ97 ዓ.ም. በፊት ምን ያህል ስለ ፖለቲካ ፓርቲዎች ግንዛቤ እንደሌላቸው በመፅሐፋቸው ውስጥ በተለያዩ ገፆች ያሰፈሯቸውን ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ማንበቡ በቂ ግንዛቤ የሚሰጥ ይመስለኛል፡፡ “ከ1997 ዓ.ም. ምርጫና ለዚህም ዝግጅት መደረግ ከጀመረበት ጊዜ በፊት የነበረውን የተቃዋሚዎች ሁኔታ ጠልቄ አላውቅም፡፡” (ገፅ 138)

“---- ወደ ፖለቲካው ሙሉ በሙሉ እስከ ገባሁበት እስከ 1997 መጀመሪያ ድረስ እንደማንኛውም ዜጋ ጋዜጣ በማንበብ ከማገኛቸው መረጃዎች ውጭ (ስለተቃዋሚዎች) ብዙም የማውቀው ነገር አልነበረም፡፡” (ገፅ 188)

እነዚህን አረፍተ ነገሮች የሚያነብ ማንኛቸውም ሰው ዶ/ር ብርሃኑ በጥልቀት የማያውቁት ጉዳይ ላይ ስሜታዊ አስተያየት እየሰጡ መሆናቸውን በቀላሉ የሚገነዘብ ይመስለኛል፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ ስለፖለቲካ ፓርቲዎች አለማወቅ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ከአገሪቱ ወቅታዊ ሁኔታ ጋር ምን ያህል ተራርቀው እንደኖሩ የሚያሳዩ የተለያዩ ምሳሌዎች ከራሳቸው መፅሐፍ ውስጥ አንብቦ መረዳት ይቻላል፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ አገሪቱ ውስጥ ሰዎች ድብደባ /Torture/ የሚፈፀምባቸው መሆኑን

ለመጀመሪያ ጊዜ ያወቁት በ93 ዓ.ም. ማዕከላዊ በታሰሩበት ወቅት ሌሊት ላይ አንድ እስረኛ ሲገረፍና ሲጮህ በመስማታቸው እንደሆነ፣ በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ሥርዓቱ ስለሚፈፅመው በደልና ሕዝቡ ውስጥ ስላለው መማረር ያወቁት አንድ የኦነግ አባል ተብለው እዛው ማዕከላዊ የታሰሩ አዛውንት የሚናገሩትን ከሰሙ በኋላ እንደሆነ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በኢህአዴግ ላይ የነበረውን ተስፋ እያጣ የመጣው ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት በኋላ እንደሆነ፣ ከምርጫ 97 በፊት የኢትዮጵያ ሕዝብ ለእውነተኛ የዴሞክራሲ ግንባታ የበቃ ህብረተሰብ እንዳልሆነ አድርገው ከሚያምኑት ሰዎች ውስጥ እርሳቸው አንዱ እንደነበሩ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በነፃነትና በአንድነት የመኖር የለውጥ ፍላጐት ለመጀመሪያ ጊዜ ያሳየው በግንቦቱ ምርጫ እንደሆነና በአጠቃላይም ሁሉም ነገር ተጀምሮ የተጨረሰው እርሳቸው ትግሉን በተቀላቀሉበት በምርጫ 97 እንደሆነ የሚገልፁ ተደጋጋሚ አስተያየቶችን ሰጥተዋል፡፡

የዛሬ 5 ዓመት ገደማ ይመስለኛል ዶ/ር ብርሃኑ የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናትን ለመጀመሪያ ጊዜ ጐብኝተው ሲመለሱ አንድ የጋዜጣ ቃለ መጠይቅ መስጠታቸውን አስታውሳለሁ፡፡ በዚያ ቃለ መጠይቃቸው " ኢትዮጵያ ውስጥ ልመና በህግ መከልከል አለበት" የሚል አስተያየት ሰጥተው ነበር፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ ይህንን መሰል የኢትዮጵያን ሕዝብ የኑሮ ደረጃ ያላገናዘበ ስሜታዊ አስተያየት በመስጠታቸው ብዙ ሰዎች ይተቿቸው ነበር፡፡ እኔ ግን ሰውየው ይህንን አስተያየት የሰጡት ላሊበላን በጐበኙበት ወቅት ለእድገትና ለስልጣኔ መኖር ካላቸው ቁጭት የተነሳ ነው በሚል አስተያየታቸውን በበጐ ለማየት ሞክሬ ነበር፡፡ ዛሬ ግን ይህንን መፅሐፋቸውን ካነበብኩ በኋላ ሰውየው ከአንድ ቅፅበታዊ ጉዳይ ላይ በድንገት ተነስተው በቀላሉ ወደ ሌላ አጠቃላይ ድምዳሜ ላይ መሸጋገር የተለመደ ባህሪያቸው መሆኑን ተገንዝቤአለሁ፡፡ የባህሪ ጉዳይ ባይሆን ኖሮ 14 ዓመታት ሙሉ የተሰራውን ስራና የነበረውን ፖለቲካዊ ሁኔታ ሁሉ በዜሮ አባዝተው የአንድ አመት ቅፅበታዊ ክስተት - በዋናነትም የግላቸው ውጤት አድርገው ባላቀረቡት ነበር፡፡ በአጠቃላይ የዶ/ር ብርሃኑን መፅሐፍ ከጅምሩ እስከ መቋጫው ይዞት የሚዘልቀው ሃሣብ - ምርጫ 97 የሁሉም ነገር መጀመሪያም መጨረሻም መሆኑን ነው፡፡ በእርሳቸው እምነት - የኢትዮጵያ ሕዝብ እና ኢህአዴግ የተቃቃሩት፣ ፖለቲከኞችና የፖለቲካ ድርጅቶች ዓላማና ራዕይ ይዘው መታገል የጀመሩት፣ ሕዝብ የአንድነትና የነፃነት የለውጥ ፍላጐት ያደረበት፣ ዜጐችም በዓላማቸው ምክኒያት መታሰርና መገደል የጀመሩት፣ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ኢህአዴግን ደፍረው በውይይት መድረክ ላይ መተቸት የጀመሩት በምርጫ 97 ወቅት ነው፡፡

ዶ/ር ብርሃኑ ይህንን ሁሉም ነገር የተጀመረው በምርጫ 97 ነው የሚለውን አስተሳሰባቸውን አቋም አድርገው እስከ መጨረሻም ቢከራከሩበት መልካም ነበር፡፡ ነገር ግን ከላይ በተጠቀሱት አባባላቸው ለማሳየት እንደተሞከረው "ከምርጫ 97 በፊት ስለተቃዋሚዎች የማውቀው ነገር አልነበረም" በማለት እራሳቸውን በራሳቸው ደጋግመው ሲቃረኑና ባላወቁት ጉዳይ ላይ አስተያየት እየሰጡ መሆናቸውን በራሳቸው ላይ ምስክርነት ሲሠጡ ይታያሉ፡፡

ይህንን የመጀመሪያ ክፍል ትችቴን ለመቋጨት - ዶ/ር ብርሃኑ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ዓላማና ራዕይ ያለው የፖለቲካ ድርጅት ሆኖ የተቋቋመው በእርሳቸው የሚመራው ቀስተ ዳመና መሆኑን ለማሳመን ያደረጉት ጥረት ምን

ያህል መሠረተ ቢስ መሆኑን በመፅሐፋቸው ላይ ባሰፈሯቸው እርስ በርሳቸው የሚጋጩ ሁለት ሃሳቦች ለማየት እንሞክር፡፡

በመፅሐፋቸው ክፍል 5 ገፅ 257 ላይ እንዲህ ይላሉ ዶ/ር ብርሃኑ - "ቀስተ ደመና ቅንጅትን የማቋቋም ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ ከመጀመሩ በፊት ባደረጋቸው ሥፊ ውይይቶች በመጀመሪያ የዚህን የአማራጭ ራዕይ እጥረት (vision Deficit) መሸፈን እንዳለበት ነበር የተገነዘበው፡፡ ይህን ለማድረግም (በዜግነት እኩልነት ላይ የተመሠረተ የአገር አንድነት) ወደፊት በኢትዮጵያ መመስረት ያለበት ሥርዓት የማዕዘን ድንጋይ መሆን እንዳለበት ግልፅ እና ደፋር (Bold) አቋም ወሰደ፡፡ ይህ ከሞላ ጐደል አብርሃም ሊንከን በአሜሪካ የእርስ በእርስ ጦርነት ጊዜ የባርነት ስርዓቱንም ሆነ የአሜሪካንን መከፋፈል በመቃወም ነፃነትና አንድነት የማይነጣጠሉበት አገር መመስረት ሲሉ ካቀረቡት ራዕይ ጋር ይመሳሰላል፡፡" (257)

በዶ/ር ብርሃኑ እምነት ይህ "ግልፅና ደፋር" ብለው ያቀረቡት "በዜግነት እኩልነት ላይ የተመሠረተ የአገር አንድነት" የሚለው አስተሳሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ትግሉ ጐራ የመጣው በ97 ዓ.ም. በቀስተ ደመና አማካኝነት ነው፡፡ መቼም ዶ/ር ብርሃኑ ለአለፉት 14 ዓመታት በትግሉ ውስጥ ከነበሩት ፓርቲዎች ውስጥ ተሳስተው የአንዱን የፖለቲካ ድርጅት ፕሮግራም እንኳን አንብበው ቢሆኑ ኖሮ እንዲህ አይነት ደፋርና የሚያስገምት አስተያየት ባልሰጡ ነበር፡፡ በእውነት ዶ/ር ብርሃኑ በተደጋጋሚ "ከምርጫ 97ዓ.ም. በፊት ስለተቃዋሚዎች አላውቅም ነበር" በማለት የሰጡት አስተያየት እውነትና ከልብ እንደነበር ከዚህ በላይ ማረጋገጫ ያለ አይመስለኝም፡፡ ይህ እውነት ባይሆን ኖሮ ለአለፉት 14 ዓመታት ተቃዋሚዎች በየመድረኩ የመዝሙር ያህል ስናቀነቅነው የከረምነውን "በዜግነት እኩልነት ላይ የተመሠረተ የአገር አንድነት" የመፍጠር አጀንዳ እንደ አዲስ ነገር "ግልፅና ደፋር አቋም" በማለት አጋነው ሊያቀርቡት ባልደፈሩ ነበር፡፡ እኔ እስከማውቀው ድረስ ኢዴአፓ-መድህን "በዜግነት እኩልነት ላይ የተመሠረተ የአገር አንድነት እንዲፈጠር አጀንዳ ቀርፆ መታገል የጀመረው ዶ/ር ብርሃኑ ወደ ትግሉ ከመምጣታቸው ከ6 ዓመት በፊት ነው፡፡

ዶ/ር ብርሃኑ ይህን በማለት አላበቁም፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ በቀስተ ደመና አማካኝነት መጣ የተባለው አስተሳሰብ ምን ያህል የቅንጅቱ አስተሳሰብ ለመሆን እንደበቃ ለማሳየት

ከላይ ከጠቀስኩት አንቀፅ ጋር በማያያዝ የሚከተለውን አባባል ተጠቅመዋል - "---ይህ ግልፅ ራዕይ በቅንጅት አባል ድርጅቶች መካከል እያደር እየሰረፀ ሄዶ በምርጫ 97 ዘመቻ ወቅት ከፍተኛ ቅስቀሳ የተካሄደበት በሰፊ የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ ተቀባይነት ያገኘና የማታለያ ብቻ ሣይሆን በብዙ የቅንጅት አባሎች ዘንድ ቀስ እያለ ስር የሰደደ እምነት የሆነ ራዕይ ነበር፡፡" (ገፅ 257)

በእውነት ይህንን አረፍተ ነገር ዶ/ር ብርሃኑ መፅሐፍ ላይ ሳነብ- ሰውየው ስለምን እንደሚያወሩ በጣም ግራ ነው የገባኝ፡፡ እኔ እስከማውቀው ድረስ አንድም በራዕይ ደረጃ ሊጠቀስ የሚችል አዲስ አስተሳሰብ የያዘ ሰነድ በቀስተ ደመና በኩል ቀርቦ በቅንጅትተቀባይነት ሲያገኝ አላየሁም፡፡ የቅንጅቱን ራዕይ በዝርዝር

የሚያመላክተውና ቅንጅት ለምርጫ ዘመቻ ይዞት የቀረበው የምርጫ ማንፌስቶ ሙሉ በሙሉ በኢዴአፓ-መድህን ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው፡፡ ኢዴአፓ-መድህን ይህንን ሰነድ ከ500 በላይ ገፆች ካሉት የፖለቲካ ፕሮግራሙ የትንታኔ ሰነድ ላይ ጨምቆ በማውጣት አዘጋጅቶ ያጠናቀቀው ደግሞ ቅንጅቱም ሆነ ቀስተ ደመና ከመመስረታቸው ከሁለት ዓመታት በፊት በ1995 ዓ.ም. ነው፡፡ ከዚህ በኢዴአፓ-መድህን በኩል ተዘጋጅቶ ከቀረበው የቅንጅቱ የምርጫ ማንፌስቶ በተለየ የቅንጅት ራዕይ የሰፈረበት ሌላ ሰነድ ቅንጅቱ ኖሮት ስለማያውቅ ዶ/ር ብርሃኑ በከፍተኛ መመፃደቅ "አዲስና ደፋር" በማለት የሚያወሩለት ራዕይ የትኛው እንደሆነ ለኔ ግልፅ አይደለም፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ የቅንጅቱ የምርጫ ማንፌስቶ የተዘጋጀው በቀስተ ደመና በኩል ነው ብለው ለመከራከር እየሞከሩ ነው እንዳይባል በዚሁ መጽሐፋቸው ሌላ ክፍል ላይ የቅንጅቱ ማንፌስቶ በኢዴአፓ-መድህን በኩል ተዘጋጅቶ የቀረበ ስለመሆኑ በሚከተለው መልኩ ገልፀዋል፡፡

"--- የምርጫ ማኒፌስቶውን ማዘጋጀት ብቻ ሳይሆን በመጨረሻ የያዘውን ቅርጽም ይዞ እንዲወጣ በዚህ ስራ ላይ የተሰማሩ የኢዴአፓ-መድህን ሰዎች በእውነት ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ እነማን እንደሆኑ ስለማላውቅ ነው ስማቸውን ያልጠቀስኩት፡፡ ማኒፌስቶው በብዙ መልኩ በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጀ የኢህአዴግን አፍ ያዘጋ ዶክመንት ነበር፡፡ እኔ እስከማውቀው በዚህ የምርጫ ጊዜ ከቅንጅት ሌላ የምርጫ ማኒፌስቶ ያወጣ ድርጅት የለም፡፡" (ገፅ 268)

እንግዲህ በ97 ዓ.ም. ምርጫ ቅንጅት ለተለያዩ የክርክር መድረኮችም ሆነ ለመስክ ላይ ቅስቀሳዎች የሃሣብ ምንጭና መነሻ አድርጎ የተጠቀመው ይህንን የምርጫ ማንፌስቶ ነው፡፡ ይህንን ሃቅ ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ዶ/ር ብርሃኑ አምነው ከተቀበሉ በኋላ ለምን የቅንጅቱ የራዕይ ምንጭ እሳቸውና ቀስተ ደመና እንደሆኑ አድርገው አንባቢን ለማሳመን እንደሚሞክሩ አልገባኝም፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ እንደሚሉት ቀስተ ደመና ከኢዴአፓ-መድህን የተሻለ "አዲስና ደፋር" ራዕይ ይዞ ቀርቦ ቢሆን ኖሮ ለቅንጅቱ ማኒፌስቶ ተቀባይነት የሚያገኘው ሰነድ የኢዴአፓ-መድህን መሆኑ ቀርቶ የቀስተ ደመና ይሆን ነበር፡፡ ስለዚህ ተገቢ ያልሆነ የታሪክ ሽፍጥና ቅሚያ ውስጥ እንግባ ካልተባለ በስተቀር ቅንጅትን የጠራ ራዕይ ባለቤት ያደረገው ኢዴአፓ-መድህን እንጂ ቀስተ ደመና አይደለም፡፡

ከዚህ አዲስ ራዕይና አስተሳሰብ ይዞ ከመምጣት ጋር በተያያዘ ቀስተ ደመና ቀድሞ በአገራችን ያልነበሩ በርካታ አዳዲስ የትግል ስልቶችን ይዞ እንደሚመጣ ዶ/ር ብርሃኑ በመፅሐፋቸው በሰፊው አትተዋል፡፡ ለምሳሌ ያህል ዋና ዋናዎቹን ነጥቦች ለመጥቀስ ብሞክር ከኩርፊያና ከጥላቻ የፀዳ ሰላማዊ ትግል ማድረግ፣ የትግራይን ሕዝብና ህውሃትን ነጣጥሎ ማየት፣ ውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲን ማስፈን፣ ከብሔረሰባዊ አደረጃጀት የዘለለ ህብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት መከተል፣ በምርጫ ወቅት የተቃዋሚዎች እርስ በርስ ያለመወዳደር አሰራርና ኢህአዴግን በግልፅ መድረክ የመተቸት ድፍረት መታየት የተጀመረው ቀስተደመና ትግሉን በተቀላቀለበት በምርጫ 97 እንደሆነ አድርገው ገልፀዋል፡፡ መቸም 14 ዓመት ሙሉ ኩረንቲና ፖለቲካን በሩቅ በሚል አስተሳሰብ እራሱን ከፖለቲካ ትግሉ አግልሎ ከቆየ በኋላ በምርጫ 97 ዓ.ም. ትግሉን በስሜት የተቀላቀለ ሰው ካልሆነ በስተቀር ስለተቃዋሚ ፓርቲዎችና ስለፖለቲካ ትግሉ መጠነኛ ግንዛቤ ያለው ማንም ሰው

እነዚህ ከላይ የጠቀስኳቸው ነጥቦች ቢያንስ ለአለፉት 7 ዓመታት ከኢዴአፓ-መድህን አጠቃላይ የትግል እንቅስቃሴ ጋር የተቆራኙ ጉዳዮች መሆናቸውን ለመገንዘብ የሚሳነው አይመስለኝም፡፡ ኢዴአፓ-መድህን ከኩርፊያና ከጥላቻ የፀዳ ሰላማዊ ትግል በአገራችን መካሄድ አለበት ብሎ በመንቀሳቀሱ ምክንያት ምን ያህል በውጭ አገር የሚገኙ እነ ኢህአፓን የመሰሉ በትጥቅ ትግል የሚያምኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ለአለፉት 7 አመታት የአሉባልታ ዘመቻ ሲያካሂዱበት እንደቆዩና ይህ ዓይነቱ ፀረ-ኢዴአፓ-መድህን የአሉባልታ ዘመቻቸው ዛሬም እንዳላቆሙ ለማንም ግልፅ ነው፡፡ ኢዴአፓ-መድህን የትግራይን ሕዝብና ህውኃትን ለያይቶ በማየት ረገድ ቢያንስ ከ1992 ዓ.ም.ቱ የአገራችን ብሔራዊ ምርጫ ጀምሮ ምን ያህል የጠራ አቋም ይዞ እንደተንቀሳቀሰና በዚህም ምክኒያት በ1994 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ በመቀሌ ከተማ ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ የታየበት ውጤታማ ሕዝባዊ ስብሰባ ያደረገ ተቃዋሚ ፓርቲ መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ይመስለኛል፡፡ ውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲን ማስፈንን በተመለከተም ኢዴአፓ-መድህን ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ በየሁለት ዓመቱ ጠቅላላ ጉባዔውን በማካሄድና በየጊዜው የአመራር ለውጥ በማሳየት፣ ከዚያም በላይ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የፓርቲ መሪነት ስልጣን በአንድ ሰው ከ4 ዓመት በላይ እንዳይያዝ በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የደነገገና ከዚህም በተጨማሪ አሁንም በአገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ አራት ፓርቲዎች ወደ አንድነት የመጡበት የውህደት ፋና ወጊ የሆነ ፓርቲ ነው፡፡ በብሔረሰባዊ ማንነት መደራጀት የፖለቲካ ፋሽን በሆነበትና ከእንግዲህ በርዕዮተ ዓለም ዙሪያ መደራጀት በኢትዮጵያ ተቀባይነት የለውም ተብሎ በሚታመንበት ጊዜም ኢዴአፓ-መድህን ህብረ-ብሔራዊ አደረጃጀትን በመከተልና ከፍተኛ የሕዝብ ተቀባይነትን በማግኘት ህብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት ዛሬም በሀገራችን ተቀባይነት ያለው ስልት መሆኑን በተግባር ያረጋገጠ ፓርቲ ነው፡፡

በምርጫ ወቅት እርስ በርስ አለመወዳደርም ቅንጅት ከተመሠረተ በኋላ የተጀመረ አዲስ ነገር አይደለም፡፡ መኢአድና ኢዴአፓ-መድህን የተቃዋሚዎች እርስ በርስ መወዳደር ምን ያህል ጐጅ መሆኑን በቂ ትምህርት ማግኘት የቻሉት ከ7 ዓመታት በፊት በ1992 ዓመቱ ብሔራዊ ምርጫ ወቅት ነበር፡፡ በዚያ ምርጫ ሁለቱ ድርጅቶች እርስ በርስ በመወዳደራችን ምክኒያት ለኢህአዴግ የተሻለ የአሸናፊነት እድል በመስጠት እራሳችን ጐድተን ስለነበር በሚቀጥለው አመት በተካሄደው የወረዳና የቀበሌ ምርጫ በምርጫው ተዋዳዳሪ የነበርን አራት ፓርቲዎች አንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች የትብብር መድረክ የሚባል አካል አቋቁመን በምርጫው ተወዳደርን፡፡ በዚህም ምክንያት ኢህአዴግ በቀላሉ ምርጫውን የማሸነፍ እድል እንደሌለው በማወቁ አይን ያወጣ ማጭበርበርና አፈና በዚያ ምርጫ ላይ ፈፀመ፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ በመፅሐፋቸው ውስጥ በተደጋጋሚ እንደጠቀሱት ከፍተኛ ዲፕሎማሲያዊ ጫና በኢህአዴግ ላይ የውጭ መንግሥታት ማድረግ የጀመሩት ከዚህ ምርጫ በኋላ ነበር፡፡ ምርጫ 97 ከአለፉት ምርጫዎች በተሻለ ሁኔታ ለቀቅ - ብሎ የተገኘውም በዋናነት በዚህ ምክኒያት ነው፡፡ ስለዚህ መኢአድና ኢዴአፓ-መድህን የቱንም ያህል በመካከላችን መቃቃር ቢኖር ወደድንም ጠላንም ለየእራሳችን ጥቅም ስንል (ቅንጅት ተፈጠረም አልተፈጠረም) ዘግይቶም ቢሆን በምርጫ 97 እርስ በርሳችን ላለመወዳደር መወሰናችን የማይቀር ነበር፡፡ በእርግጥ የቅንጅት መፈጠር የምርጫ ዘመቻውን በጋራ ለማካሄድና በአንድ የጋራ የምርጫ ምልክት ለመወዳደር እንድንችል በማድረግ ረገድ ያበረከተልን

አስተዋፅኦ የሚናቅ አይደለም፡፡ በውይይትና በክርክር መድረክ ላይ ኢህአዴግን በድፍረት መተቸት የተጀመረውም ዶ/ር ብርሃኑ እንደሚሉት በምርጫ 97 አይደለም፡፡ መጠኑ ከ97ዓ.ምቱ ምርጫ ያነሰ ቢሆንም ተቃዋሚዎች በክርክር መድረክ ላይ ኢህአዴግን እራቁቱን ማስቀረት የጀመርነው ከ92 ዓ.ም.ቱ ብሔራዊ ምርጫ ጀምሮ ነው፡፡ በተለይም ኢ.ዴ.አ.ፓ-መድህን እንደሌሎች ፓርቲዎች "የእናቴ መቀነት አሰናከለኝ" እያለ ከክርክር መድረኮች እራሱን ሳያገል ራዕይና አቋም ያለው ፓርቲ መሆኑን ለሕዝብ ማሳየት የጀመረው ቀስተደመና የሚባል ፓርቲ ከመፈጠሩ ከ6 ዓመታት በፊት ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ሳይቀር በአደባባይ ከስልጣን እንዲወርዱ በመጠየቅ ኢ.ዴ.አ.ፓ-መድህን ምን ያህል የህብረተሰቡን የፍርሃት ድባብ ለመስበር ቀዳሚ ፓርቲ እንደነበር ለምን ዶ/ር ብርሃኑ ማወቅ እንዳልቻሉና ሁሉንም ነገር በእርሳቸውና በቀስተ ደመና ጊዜ የተጀመረ አድርገው ለማቅረብ እንደሚፈልጉ ለእኔ በጣም አስገራሚ እንቆቅልሽ ነው፡፡ የቀድሞ የኢ.ህ.አ.ፓና የመኢሶን አባላት ከ20 ዓመት በኋላ ስለ ድርጅቶቻቸው ታሪክ የፃፏቸውን መፅሐፍት ሳነብ በሁለት ድርጅቶች መካከል የሚታየው የታሪክ ባለቤትነት ሽሚያ በጣም አድርጎ ያስገርመኝ ነበር፡፡ ነገር ግን የምርጫ 97ዓ.ም. ትዝታ ከህሊናችን ገና መደብዘዝ ባልጀመረበት በአሁኑ ወቅት ትግሉን ከተቀላቀሉ ገና አንድ አመት ያልሞላቸው ዶ/ር ብርሃኑ የሁሉም የትግል ታሪክ ባለቤት እርሳቸውና ቀስተ ደመና መሆናቸውን ሊነግሩን መድፈራቸውን ሳይ የኢ.ህ.አ.ፓና የመኢሶን ታሪክ ፀሐፊዎችን በልቤ ማሩኝ ብያቸዋለሁ፡፡ ስለዚህ ዶ/ር ብርሃኑ ቅንጅት ይዞት የቀረበው ራዕይ የማን ነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ሲሞክሩ እውነቱን ተናግረው ኢ.ዴ.አ.ፓ-መድህን የሚገባውን ምስጋና እንዲያገኝ ለማድረግ ባይፈልጉ እንኳ ቢያንስ የቅንጅቱ ራዕይ "የጋራችን ነው" ብለው ቢፅፉ በተወሰነ ደረጃ የጨዋ አባባል ይሆን ነበር፡፡

ይቀጥላል…